# 'የስንብት ቀለማት' እንደ ብሔርተኛ ሀቲት (Nationalist discourse)

(በመፅሐፉ ድህረ ቃል ከቀረበው ዳሰሳ የተወሰደ)

**በቴዎድሮስ ገብሬ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)**

የሚት (Myth) በተለይም የፖለቲካ ሚት ተመራማሪዎች (ለምሳሌ Anthony Smith, 1999) እንደሚነግሩን፤ ያለ ሚት (Myth) የቆመ አንድም ሀገር የለም። በዚያው መንገድ የክብረ ነገሥቱ፣ የሰለሞን-ሳባ ትውፊት፤ ረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ የተመሰረተበት የፖለቲካ ሚት፤ አውራ ተረክ (Grand Narrative) ነው።

የታሪክና የፖለቲካ ምርምሮች እንደሚያስረዱን ቅድመ ጣሊያን ወረራ በአንድ በኩል፣ በሰለሞን-ሳባ ልማድ የታሰረው ቤተ መንግስት በሌላ በኩል፣ የዚህ ልማድ አስቀጣይ የሆነችው ቤተ ክህነት በትብብር በ "ብሔረ ኢትዮጵያ" አምሳል አገሪቱን አንድ አድርጎ ለመቅረፅ የሚባትሉበት ጊዜ ነበር።

የኢትዮጵያ "ኪነ ጥበብ" በተለይ እስከ 1950ዎቹ መግቢያ ድረስ ባለው ጊዜ ይህንን ሚት፣ መንግስት መር የሆነውን ብሔርተኝነት (State led nationalism) ለማቀንቀንም ይባል ጠብቆ ለማኖር ምቹ በመሆኑ ይታወቃል። በአጠቃላይ እስከ 1950ዎቹ መባቻ ያለው ዘመን ኪኑም ሆነ ሚቶሎጂው ለሮማንሱ ማበብ "ለም መሬት" ሲሆን ሮማንሱም የገዢውን መደብ ፈቃድና ፍላጎት ለማስፈፀም ፍፁም የተመቸ ርዕዮተ ዓለማዊ መሣሪያ ነበር።

የኢትዮጵያ ስነ ፅሑፍ ይህንን አይነቱን ሮማንስ ለማቀንቀን ምቹ መድረክ የመሆኑን ያህል የተግዳሮቱም ምንጭ እንደነበር ማወቅ ይቻላል። ዳሩ ግን ከ "አረመኔው" ይልቅ "ለክርስቲያኑ"፣ ከቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል አብልጦ ለሰሜኑ የሚያደላው ይህ 'ጥገናዊ ለውጥ' ለዘመኑ የሚመጥን አልሆነም።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ እንደ አለቃ ታዬ ገብረ ማርያም ባሉ፤ በባህላዊው ትምህርት ባለፉና እውጭ ደርሰው በተመለሱ ቀና አሳቢዎች፤ ኋላም ገብረ ሕይወት ባይከዳኝን እና ታምራት አማኑኤልን በመሰሉ የምዕራቡን ዓለም ትምሕርት ጠንቅቀው በሚያውቁ ጥቂት ኢትዮጵያዊ ምሁራን ፈተና ገጥሞታል።

ሮማንሱ የማይወጣው ፈተና ውስጥ የገባው በ 1950ዎቹ መግቢያ፤ በተለይም በ1953ቱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራና እሱን ተከትሎ በተነሳው የተማሪዎች ንቅናቄ ነው።

ከፋቱ ንቅናቄው ፍፁም ከመፅነፉ የተነሳ የየሰዉን ልብ በአናርኪዝምና በኒሂሊዝም መንፈስ ሞላ። ማፍረስ ብቻ፣ መንቀል ብቻ ግቡ ሆነ። ነፍስ ያላወቀው ትውልድ በነቀለው እሴት ፋንታ አዲስ አልተከለም። ባፈረሰው ሮማንስ ምትክ ሌላ ሮማንስ አላበጀም። (ማርክሲዝም ሌኒንዝም አዲስ ሮማንስ ነው ካላልን በስተቀር)

የአገር ያለ ሚት መቅረት በዘይቤ ተራ 'የነፍስ ከስጋ መለየት' ነው። (ሚት በብዙዎቹ ሚቶግራፈሮች "necessary fiction" አልያም "Supreme fiction" ተብሎ ነው የሚገለፀው።) ኢትዮጵያውያን ዛሬ ከገጠሙን ሰብአዊ ድቀቶች፣ የባህልና የመንፈስ ንቅዘቶች ብዙዎቹ፤ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ከዚህ ጋር የሚዛመዱ ይመስላሉ።

የአዳም ሙከራ እንግዲህ ከኢትዮጵያውያን እሴቶች ቀስሞ በነደፈው አዲስ ሚት የኢትዮጵያን ትንሳዔ ማብሰር ነው። ትንሣዔው ከላይ ነድፌ ለማሳየት እንደሞከርኩት ለረዥም ዘመን ሲቀነቀን፣ ሲታደስ፣ ሲጠገን ኖሮ በመጨረሻ የፈረሰውን አውራ ተረክ (የሶሎሞን-ሳባ-ምኒልክ ትውፊት በመንኮቢያ-ምትኬ-ማኩታ ትውፊት **በመተካት** የሚከናወን ይሆናል። ማክዳና ምትኬ ትይዩ ናቸው የምለው በዚህ መስመር ጭምር እያሰብኩ ነው።

'የስንብት ቀለማት ሚት አዲስነት ምን ላይ ነው?' የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል።

እርግጥ ነው ስንዝሮ ከተረት አለም የተቀዳ ባሕርይ ነው። (በተራኪው ባይነገረን ማወቅ አለመቻላችንን ግን ልብ ማለት ይገባል)። ድንግልናና በድንግልና መውለድ ነባር ሚታዊም ኪናዊም መባያዎች (motifs)፣ አልያም ገዢ ተረኮች (master

narratives) ናቸው ወዘተ . . . ማንም ከዚህ እስር አያመልጥም። የመንኮቢያ-ምትኬ-ማኩታን ሚት አዲስነት ብዙ ሳንሄድ በሁለት ጉዳዮች ብቻ ማረጋገጥ እንችላለን። አንደኛ በባለ ገድሎቹ ታሪክ (story)፣ ሁለተኛ በካራክተራይዜሽኑ። የስንዝሮን ታሪክ በስንጣሪው እንኳን በዚህ መንገድ ማን ሰምቶት ያውቃል? ይሄ ዳግም ልደት ነው።

ካራክተራይዜሽን የማስተማሰል (representation) ጣጣ ነው። እንደ ሸረሪት ድር ተጠላልፎ በአንድ ሺህ ገፅ ያህል የሰፈነውን አስተማስሎ እንደ ሰነፍ ቸል ብለን ምትኬን እንከተል ብንል እንኳ የተስተማሰሉት እሴቶች እጅግ እንግዳ ናቸው።

ለምሳሌ፣ በየሚቲክ ትረካው በደናግል-እናትነት በተቀረፁ ሴቶች ውስጥ የምንመለከተው እንስታዊ ውበት፣ ልስላሴና ስስነት (the convention of femininity) በምትኬ ዓለም ውስጥ ተፈልጎ ይገኛል? በመልከአ ማርያም ደንብ የተነደፈው "መልከአ ምትክ" ጡቶችሽ፣ ወገብሽ፣ ወዘተ በሚልበት ደንብ ሎሚ ተረከዝሽ አይለንም።

የተረከዟን ንቃቃት፣ የንቃቃቷን በአፈርና ዓመድ ትግግዝ መደፈን ገላልጦ ያሳየናል። ይህቺ ሴት 'የንፉግ ምፅዋት' (ከንፈር መምጠጥ) በሚቸርበት አገር ያላትን በልግስና እያካፈለች 'ክፉ ሳትሆን ክፉ ለመምሰል ትጣጣራለች' (ገፅ 612)

ተቃርኖውን ማጤን ነው . . .

ከቤ፤ እንስትነት ከተባዕትነት ጋር ተስማምተው በሕብረት የተጠለሉባት ሴት ናት። (ለተኮላና ለጅማ ግጭት ምክኒያት መሆኗን ማሰብ ነው)።

ስንዝሮ ደግሞ የዚህችን ሴት ውበት በሥራ መስፈሪያነት እያገገ ማድነቁ አለምክኒያት አይመስለኝም። በሥራ የደደሩ ባቶቿ፣ ሥራ ያጠነከረው ወገቧ፣ ሥራ ያደለደለው ክንዷ . . .። በምትል ፍፁም የሚሸነፈው ስንዝሮ ሌላው የኢትዮጵያዊነት መስፈሪያችን ነው።

ስንዝሮ የጎሳ ቀለም የሌላት አዲስ አበባ ገብቶ እስኪገራ ድረስ በ place located ያለመሆኑ አንደኛው ፋይዳ ይሄው ነው።

በመንኮብያ-ምትኬ-ማኩታ ትውፊት ላይ የሚመሰረተው አዲሱ የሀገራችን ሮማንስ ሃይማኖቱም፣ ብሄርተኝነቱም "ኢትዮጵያዊነት" ነው።

ነባሮቹ የኢትዮጵያ ትዕምርቶች - ጤፍና የጤፍ እንጀራ፣ አደይ አበባ፣ የመስቀል ወፍ፣ ብራና ወዘተ በአዲስ ጥምቀት አዲስ ምንነትን ይቀዳጃሉ።

ታላቁ የሙዚቃ ሊቅ ማሕሌታይ ያሬድ (በእሱ ትይዩ ሌሎች ሊቃውንት አበውንና እመውን ማሰብ ይቻላል) የሃይማኖት ቀለሙ ተራግፎለት የመንኮቢያ ተማሪ ይሆናል።

ይህ ሁሉ የኪነት ድካም አዲስ ብሔራዊ ምንትነት የመገንባት፣ እድዲስ አገር የመመስረት ጣጣ ነው። እናም ድርሰቱን እንደ ብሄርተኛ ሀቲት (as a nationalist discourse) ልንቆጥረው እንችላለን።

ይህ ሁሉ ሕማምና ጭንቅ ለምን? ከነጭራሹስ የአገር (state) ምስረታ የከያኒ ጉዳይ (በፖለቲካው ቋንቋ "mandate" ነውን? የዚህ መልስ 'ምን ጥያቄ አለው!' የሚል ነው። በነገረ ኪን ረገድ ብዙ ሊባልበት ይችላል። (እንደውም አበይት ከያኒያን (major artists) የኪነታቸውና የተውህቦአቸው ዳርቻ ላይ መድረሳቸው የሚረጋገጠው በእንዲህ ያለው ተግባር መሆኑን ብዙዎች ይመሰክራሉ)።

ለጊዜው ጉዳያችን ማሕበራዊ ሳይንስ ይሁን። የማሕበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ብሔር (state) እን ብሔርተኝነት (nationalism) የሚመሰረቱበት መንገድና መንፈስ ኪናዊ መሆኑን ያስረዳሉ። ኪነት ከሌሎች ሐቲቶች በላቀ የጊዜ ጥልቀት (time depth) በመፍጠር በዚህም "ዘላለማዊነትን" ለመቀዳጀት ያስችላል።

የብሔር ግንባታ ጥብቅ መሰረትን ይጠይቃል። ይህ አይነቱ መሰረት የሚጣለው ደግሞ በጥልቅ ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው። 'ጥልቅ ጊዜ' ሁለቱን የጊዜ ፅንፎች "ሩቁን ትላንት" (ታሪክ) ከ "ሩቁ ነገ" (ትንቢት) አስተቃቅፎ የሚይዝ ነው።

"If nation states are widely conceded to be 'new' and 'historical' the nations to which they give political expression aleays loom out of an immemorial past, and, still more important, glide into a limitless future. It is the magic of nationalism to turn chance into destiny. With Debray we might say "Yes, it is quite accidental that I am born French, but after all, France is eternal" (Anderson, 1983, p.12)

ብሔር-ብሔርተኝነት በሁለቱ የጊዜ ፅንፎች በ Benedict አጠራር "immemorial past and limitless future" ላይ የተመሰረተ፣ ታሪካዊውን ከሁለንተናዊው፣ አካላዊውን ከልዕለ አካላዊው አስተባብሮ የያዘ በ Jungian አጠራር "The psychic residue" ነው። የጊዜ ምልዓቱ (temporal wholeness) ከአካላዊው እውነታ ጋር ተደምሮ ለፅንሠ ሐሳቡ 'ዘላለማዊነትን' ስለሚሰጠው ብሔር የሜታ ፊዚክስ እስረኛ፣ ሜታ ፊዚክስም በፈንታው የምናብ ተገዢ ይሆናል። ምናብ መደቡ ኪናዊ ነውና ከቶውንም ከትርጓሜና ፍካሬ ውጪ ሊታሰብ አይችልም ብዬ አምናለሁ። እንዲህ ብዬ ለማመን ደግሞ ተከታዩ የ Seamus Deane ሐሳብ ጥሩ መንደርደሪያ የሚሆነኝ ይመስለኛል።

"All nationalisms have a metaphysical dimension, for they all are driven by an ambition to realise their intrinsic essence in some specific and tangible form. The form may be a political structure or a literary tradition (1990 p."

በዚህ ሀሳብ ተስማምተን ምልከታችንን ፍካሬያዊ ካደረግን፣ በብሔረ ኢትዮጵያ ዳግም ግንባታ ረገድ ከልብ ወለዱ ሶስት ኪናዊ-ፖለቲካዊ ፋይዳዎችን መንቀስ የሚያስቸግረን አይመስለኝም።

የመጀመርያው ፋይዳ የስንብት ቀለማት በነባርና አዳዲስ ዕሴቶች ትብብር የሚታነፅ 'አዲስ ስቴት' በአማራጭነት ማቅረቡ ነው።

ከ3500 ዓመታት በላይ ዕድሜ ባለው መንኮቢያ አማካይነት ከሶሎሞን-ሳባ-ምኒልክ ሚት የሚልቅ የጊዜ ጥልቀት መፍጠሩ ሁለተኛው ፋይዳው ነው።

ሦስተኛ የመንኮቢያ-ምትኬ-ማኩታ ትውፊት (ከፍ ብለን በመቅረዟና በላስታ፣ ምትኬ ማኩታ የውርስ ትስስር ባየነው መሠረት) በማኩታ አማካይነት በተጨባጭ መጪውን ጊዜ ገደብ የለሽ "limitless future" አድርጎታል። (ነባሩ ሚት ይሄ ፈርጅ ይጎድለው ነበር)። በዚህም ከሶሎሞን-ሳባ-ምኒልክ በላቀ የጊዜ ጥልቀት "ዘላለማዊነት" ለመቀዳጀት ችሏል።